# ለመሠረታዊ ለውጥ መታገል ወይስ መገለባበጥ?

ኢትዮጵያ ሀገራችን ስላለችበት አስቸጋሪ ፖለቲካዊ፡ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሁኔታና መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ በግልም ሆነ በድርጅት ደረጃ የተለያዩ ጽሁፎች ይወጣሉ። ትክክለኛው የለውጥ መንገድ፡ መወሰድ የሚገባው እርምጃ ግን በታጋይ ፖለቲካ ድርጅቶች ዘንድ አሁንም አወዛጋቢና ወጥነት የሌለው ነው። በአብዛኛው ሁሉም የግል ሩጫውን ይዟል ወይም የአግላይነት መሳሳብ ተይዟል። የትላንት አወዛጋቢ ሙከራቸው ያስነሳውን ተቃውሞና ስህተት እያወቁ ዛሬም ሲደግሙ የሚስተዋሉ አሉ። ሰሚ ቢኖር ብዙ ተብሏል። በዚያው በበቃ ነበር። ግና የሀገር ህልውና ጉዳይ ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ የመብት፡ የሀገር ባለቤትነትና አንድነት ጥያቄ ነውና ዛሬም ማሳሰቡ አስፈላጊ ነው።

የሀገራችን ችግር ከዕለት ዕለት እየተባባሰ በሄደ ቁጥርና እጅግ አሳሳቢ፡ አስከፊ መልክ በያዘ ልክ፡ ወደ መፍትሄው እየተቃረብን በመሄድ ፈንታ ከድጡ ወደ ማጡ እየተንሸራተትን በመሄዳችን ተስፋችንን ሥጋት ውጦታል። ሥጋት ላይ የሚጥለው እስካሁን የተፈጸመው ስህተት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉት ተከታታይ ድርጊቶች ናቸው። ከዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ባሻገር ለቀጣይ የሀገሪቷ መንግሥትነት ወይም የሥርዓት ለውጥ የሚታገሉ አንዳንድ ኢትዮጵያዊ ኃይሎች እየተጓዙበት ያሉት አካሄድ ሀገሪቱን ወደ ሌላ ትርምስ ውስጥ እንዳይከታት መጠቆሙ ያስፈልጋል። የኢትዮጵያን ሕዝብ የሦስት መንግስታት ያላቋረጠ ትግል ለምን እንደሆነ በቅጡ ማጤንን ከሕዝባዊ ኃይሎች ይጠበቃል። የመንግሥት መለዋወጥ ብቻውን ለሀገርና ሕዝብ እርካታ ያመጣል፡ መፍትሄን ያስገኛል ብለን ካልን አፄው በደርግ፤ ደርግ በወያኔ፤ ሲተኩ ሀገርም ሕዝብም እፎይታን ባገኙ። በተለያዩ አገዛዞች ተመሳሳይ ድርጊት ፡ አፈና፡ ጭቆና፡ መብት እረገጣ፡ ብዝበዛ፡ ወዘተ ከቤተ መንግሥት ባለመውጣታቸውና ሕዝብ የራሴ ያለው መንግሥት የሥልጣን ባለቤት አለመሆኑ ነው ችግሩ። አንዳንድ ተቃዋሚ ኃይሎች፡ ትላንት ያልነውን ክደን ሌላ ሆነን ብንቀርብ፡ እንደፈለገን ብንገለባበጥ፡ የህዝብ "ድጋፍ" አለን ከሚል ግምት፡ በሕዝብ ጥቅምና በሀገር መቆመርና፡ መግቻ ባጣ እልህ ሀገርን ወደ ሲኦል አፋፍ መገፋፋት የታሪክ ተጠያቂ ያደርጋልና ሊያስቡበት ይገባል። ወጣም ወረደ፡ አሁን ካለው ቅጥ አምባሩ ከጠፋ የተቃዋሚዎች የርስ በርስ ችግር ለመውጣት የሚቻለው ቅንነቱ ካለ፡ መተማመንንና መግባባትን መሠረት በአደረገ መልኩ ማንንም ሳያገል ሀገር አቀፍ ውይይት ተካሂዶ ለሀገርና ሕዝብ ሲባል በጋራ ለመምከር ሲቻል ነው። አለበለዚያ ሥልጣኑም ቢያዝ ወያኔ ላይ ከተጮኸው ባላነሰ ባለተራ ከመሆን አያድንም። "የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል" እንዲሉ መሠረታዊ የሀገሪቷን አንድነት ጥያቄ ውስጥ እያስገቡ፡ በመብትና ዴሞክራሲ ስም የሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመፈናጠጥ እየተገላበጡ መደራደር አደገኛነቱን ማስገንዘብ ግድ ይላል።

የሀገራችን ኢትዮጵያና ሕዝቧ መከራና ስቃይ መቋጫ አጥቶ እናያለን። ኢትዮጵያ ዛሬም የልጆቿ አይደለችም። ዛሬም ረሀብ፡ በሽታ፡ ድህነት፡ ድንቁርና የልጆቿ ጓደኞች ናቸው። የሀገሪቷ አንጡራ ሀብት እየተዘረፈ ለባዕዳን ሲሳይ መሆን ከጀመረ በትንሹ 20 ዓመታት አስቆጥረናል። ለልማት፡ ለብልጽግና፡ ለትምህርትና ለህክምና መዋል የሚገባው ገንዘቧ ለስግብግብና አልጠግብ ባይ ገዥዎቿ መንደላቀቂያ ከመሆን አልፎ በሕዝብ ገንዘብ ሕዝብ ይጨፈጨፍበታል። አንዱ በሀገር አንድነት ስም አንድ ትውልድ ጨርሶ፡ ሀገሬ ያለውን በልቶ፡ በአንድነት ስም አንድነት ላይ ዘምቶ፡ ለዘረኛና ከፋፋይ ቡድን ተራውን ካስረከበ እነሆ 20 ዓመት ሆነው። የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ በዚህ የአገዛዝ ዘመኑ ለሕዝብ ያተረፈው ቢኖር ስቃይን፡ ድህነትን፡ ሰቀቀንን፡ ስደትንና በሽታን ለመሆኑ ሕዝብን መመልከቱ በቂ ነው። የተወለዱበትንና ያደጉበትን የጠፍር አልጋና ቁርበት እየረገጡ በሸራተንና በሌሎች ሆቴሎች ተዝናንተው እየመጡ "ሕዝቡ ደልቶታል፡ ገንዘቡን ከየት እንደሚያመጣው አናውቅም፡ ሲበላ፡ ሲጠጣ፡ ሲጨፍር ነው የሚታየው. . ." ብሎ ጥሩንባ መንፋት እራስን ካለማወቅና ማንነትን ከመዘንጋት ወይም ለሆድ ከማደር የሚመጣ ድንቁርና ነው ቢባል አግባብነት አለው።

ሀገራችን ዛሬ አግባብነት በሌለው ውል የተፈጥሮ ሀብቷና መሬቷ ለባዕዳን በወያኔ እየተቸበቸበ ነው። እኚህ ባዕዳን ኃይሎች በረዥም ጊዜ ውል በሚይዟቸው ሰፋፊ መሬቶች ያለውን የኅብረተሰብ ክፍል ያለመጠጊያ ከማፈናቀል በተጨማሪ በሀገራችን ምድር የሚያመርቱትን ወደ ሀገራቸው እያሻገሩ ሊበዘብዙን፡ ሊያራቁቱን እየተዘጋጁ ነው። የሀገራችንን ልጆች ከፈለጉ በአነስተኛ ክፍያ በባርነት ያሰራሉ፡ አለያም ከራሳቸው ሀገር የራሳቸውን ዜጋ በማስመጣት የሥራ ዕድል ያጣውን ዜጋቸውን እኛ ላይ ሥራ ይሰጡታል። የነኚህ የተለያዩ ባዕዳን ኃይላት በተለያየ አቅጣጫ ሀገራችንን መቀራመት የባህል መበከልን ያስከትላል። ወያኔ ሀገራችንን ዕዳው ለትውልድ እሚዘልቅ እንዲህ ዓይነቱ አጣብቂኝ ውስጥ መዝፈቅ ከጥንስሱ ኢትዮጵያ ለምትባል ሀገር ደንታ ስለሌለው ነው።

በፖለቲካውም መስክ ሊገባቸው ላልፈለጉ፡ ቢገባቸውም መገለባበጥ ለተጠናወታቸው በምርጫ 2002 ዓ.ም. ጭፍን አምባገነንነቱን ነግሯቸዋል። በአራት ነጥብ (።) መዝጊያው አላስጠጋም ብሏል። "እናስገባም "ተቃዋሚ"፤ እኛን ዓላሚ" ዘፍኗል። "...ዛሬ የተወሰነ ወንበር ይዘን በሚቀጥለው አምስት ዓመት እየጨመርን ቀስ በቀስ ወያኔን እናሸንፋለን..." እያሉ ይሰብኩ የነበሩ ተቃዋሚዎች ዛሬ ምን ይሉ? "አምስት ዓመት በቆጠርን ቁጥር ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እያጣን እንመጣለንና ጠንክረን እንታገል" ብለው ይመክሩ የነበሩትን ዛሬም ከቁብ ባለመቁጠር "ለሚቀጥለው አምስት ዓመት "አዲስ" ዕቅድ አውጥተናልና ጠብቁን" ባዮች ድፍረታቸው ደፋር ነው። እኚህ ታማኝ የወያኔ አገልጋዮች በተቃዋሚ ስም ተቃውሞን ሊያቀዘቅዙ ሲገለባበጡ፤ እንደ እስስት እየተቀያየሩ የአገዛዙን ዕድሜ ሊያራዝሙ፡ ይህም ከአቅም በላይ ከሆነ የከረፋውን የወያኔን ሥርዓት ከሥሩ ከመገልበጥ ይልቅ በአክሮባት ተገለባብጠው በለውጥ ስም ለቀጣይ ሂደቱ ከበሮ ሊደልቁ ሲዘጋጁ ከአሁኑ ካልታገልናቸው፡ ካልተፋለምናቸው ተፈላጊውን ውጤት ማስመዝገብ አጠያያቂ ይሆናል። የመሪነት ዕድሉን አግኝተው በሀገርና በህዝብ ላይ አላግጠውና አሹፈው የመለስ መንጋ አላስጠጋ ሲላቸው

ከተቃዋሚው ጎራ ተሰለፍን ሲሉን ተናዳፊ መሆኑ አግባብነት ባይኖረውም "ኑና ምሩን፣ ያለናንተ ትግሉ ግቡን አይመታም" ስንል አሳፋሪና አስተዛዛቢ ነው። አንዱ ኢትዮጵያን ሊበታትኑ ታጥቀው ከተነሱ ጋር ሲዶልት፣ ሌላው በተቃዋሚ ስም ጸቡ ከመለስ እንጂ ከወያኔ ሥርዓት አለመሆኑን ሲደሰኩሩ፣ በማጥ ውስጥ ሲንቦራጨቁ፣ የአንድነት ኃይሎች መሰባሰብና እራስን ለሚጠበቅብን ፍልሚያ ማዘጋጀት እንደሚገባ መገንዘብ ይኖርብናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የደረሰበትን በደልና መከራ ከአንድነቱ ጋር በማያያዝ መበታተንን ሰባኪ፣ መገነጣጠልን ናፋቂ ከሆኑ ጋር ማበር በሀገር ላይ ማፌዝና መቀለድ ነው። ትላንት ሳይመሰረት የፈረሰው አንድነት ለትብብርና ለዴሞክራሲ (AFD) ሌላ ቢቀር ለትግሉ መራዘም ያበረከተው አስተዋጽዎ የሚዘነጋ አይደለም። በሻቢያ መሪነትና በኦነግ አቀነባባሪነት ከህዝብ በስተጀርባ የተደረገው ስምምነት ፊርማ ሳይደርቅና በኅብረተሰቡ ዘንድ ያሳደረው የሞራል ድቀት ሳይሽር፣ ዛሬ በተመሳሳይ መልኩ ለመድገም መንደድረር ከአሳፋሪነት አልፎ በሀገርና ህዝብ ትግል ላይ ዱለታ ነው። የአንድነትን ኃይሎች አትጠጉኝ ብሎ አግላይ የሆነ፣ ያውም የሀገራችንን አንድነት ከሚፈታተኑ ኃይሎች ጋር ማበር ያለው ዘረኛ መንግሥት ላይ ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩም አራተኛ መንግሥት ሂደት ልናስብበት ይገባናል። <u>ወደድንም ጠላን ከእንግዲህ በሀገራችን የብሔር/ብሔረሰቦች ክልል ኢትዮጵያ እንድትሆን መታገል ይኖርብናል።</u>

አንድነት መብትን አፍኖ፣ አንድነት በብዝበዛ፣ አንድነት በጦርነት፣ ወዘተ. በአፄውም፣ በከፋ መልኩ ደግሞ በደርግ አይተናል። ስለ ሀገር አንድነት እየዘመረ፣ ባንዲራን እያውለበለበ፣ ሀገርና ትውልድ የቀበረው ደርግ፣ ለሀገርም ለልጆቿም ባለመሆኑ ነው ከ17 ዓመት ትግል በኋላ ወደ ትቢያ የተጣለው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአንድነታችንና ለነፃነታችን ቀናዒ ብንሆንም፣ በሀገራችን መብታችንን፣ ነፃነታችንን፣ እኩልነታችንን፣ ዜግነታችንን እንፈልገዋለን። ይህንን ተነፍገን፣ በእግር ብረት ታስረን፣ ኑሯችን እስር ቤት ሆኖ፣ አፋችን ተለጉሞ፣ ስደት ናፋቂ እንድንሆን ተገደን አንድነት ለአምባገነኖች ያመች እንደሁ እንጂ ለልጆቿ ሲያል ነው። ልዩነቱ የዚህ መብት እረገጣ ገፈት ቀማሽ እኔ ብቻ ነኝ፣ ሌላው ደልቶታል ከሚል አባዜ ችግሩን ከችግሩ ፈጣሪ አገዛዞች ዘለን ሀገር ላይ እናደርገዋለን። እምዬ ኢትዮጵያን ተጠያቂ እናደርጋትና መገንጠልን መፍትሄ እናደርገዋለን። ኢትዮጵያዊነት ላይ እንዘምታለን።

በኢትዮጵያ ያሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች በተለይ ከደርግ የአንድነት ዝማሬ፣ ከወያኔ የዘረኝነት አባዜ፣ ትምህርት በመቅሰም በልጆቿ እኩልነትና አንድነት ላይ የተመሰረተች ኢትዮጵያን ለመገንባት መነሳት ይኖርባቸዋል። ደርግ የብሔር/ብሔረሰቦችን ጥያቄ በጥይት ለመፍታት ያደረገው ዕቅድ፣ ያደረሰው ጉዳት ዛሬም ጠባሳው አለ። ወያኔም ይህን ችግር በከፋፍለህ ግዛና በዘረኝነት ፖሊሲ ሊፈታው አልቻለም። በደርግም ሆነ በወያኔ የመከራው ገፈት ቀማሽ አማራው፣ ኦሮሞው፣ ትግሬው፣ ወላይታው፣ ጉራጌው፣ አደሬው፣ ሱማሌው፣ ቤኒሻንጉሉ፣ ወዘተ. በጥቅሉ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ነው። የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ልጆች ታስረዋል፣ ተሰቃይተዋል፣ ተሰደዋል፣ ተገድለዋል። ሁሉም የመብት ያለህ! ያገር ያለህ! እያሉ ለዘመናት ጮኸዋል። እየጮኹም ናቸው። የአፄውና የደርግ አገዛዞች አንድን ብሔር

ሳይወክሉ የሕዝብን መብት ነፍገዋል፡ አሰቃይተዋል። የወያኔ አገዛዝ በአንድ ብሔር ስም ቢመጣም የመጣበትንም ብሔር አባላት ሳይቀር በመሠሪ ጅራፉ እየገረፈ ነው። ሁሉም ብሔር/ብሔረሰብ የተፈራረቁበትን ገዥዎች፡ ለመብትና ለሀገራዊ ግዴታው ታግሏል። ተፋልሟል። ዛሬ በመብት ስም፡ ሀገራችንን ለመበተን መነሳት የለብንም። በመብት ስም መገነጣጠልን ማራገብ አይኖርብንም። ኢትዮጵያ ሀገሬ ላለ ብሔር/ብሔረሰብ፡ አንዱ ለሌላው መብት መሟገት ያለበት ተያያዥነት ስላለው ነውና፡ የአንዱ ድል ከሌላው ሊነጠል አይችልምና፡ ለሀገርና ለሕዝብ መብት በጋራ መጮህ የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄ የሚሆነው። የኢትዮጵያን አንድነት ለሚፈታተኑ ባዕዳን ኃይሎች እራሱን የሸጠው ወያኔ ከበቂ በላይ ነው። <u>ኦሮሞው፡ ትግሬው፡ አማራው፡ ወላይታው፡ ጉራጌው፡ አደሬው፡ ሱማሌው፡ ቤኒሻንጉሉ፡ ወዘተ. በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብታችንና ለአንድነታችን ኢትዮጵያን አስቀድመን በጋራ መታገልና የጋራ ሀገራችንን ለዕድገትና ለብልጽግና ማብቃት የወደፊት ራዕያችን ቁልፉ መሆኑን ለአፍታም መዘንጋት አይገባንም።</u>

ስለ ኦነግ ስናወራ ከኦሮሞ ብሔር ነጥለን መሆን ይኖርበታል። ኦነግን የምንቃወመው ለምን ለኦሮሞ ብሔር መብት ቆሚሃለሁ ስላለ ሳይሆን፡ ኦነግ የኦሮሞን ብሔር ኢትዮጵያዊነት በመሰረዝ ባዕድ ነን፡ ከኢትዮጵያ ጋር የምንዛመደው በአዳም ልጅነት ነው፡ በግድ ተገንጥለን ኦሮሚያን ማቋቋም አለብን ብሎ የተነሳበትን አቋም እስከዛሬ ይዞ በመጓዙ ነው። ኦነግ ዛሬም ሆነ ገና ከምስረታው ሻቢያ የጠላውን ጠልቶ በመነሳቱና ኢትዮጵያ ያለውን ሁሉ በአማራ ትምክህተኝነት በመፈረጁ ከአንድነት ኃይሎች ጋር በተለይም ከኢሕአፓ ጋር ቀና ግንኙነት ሊመሰርት አልቻለም። የኦነግ አመራር የዓለምን ወቅታዊ ሁኔታና የኢትዮጵያን ሁኔታ በሚገባ በማጤንና የብዙሃኑን ኦሮሞ ብሔር ፍላጎት በመመርመር ተገቢውን የአቋም ለውጥ ተቀብሎ በኢትዮጵያዊ ድርጅትነት የኦሮሞን ብሔር ኢትዮጵያዊነት በመቀበልና የመገንጠል ፕሮግራሙን በመተው ግንባር ቀደም ሚና ሊጫወት እንደሚችል በተደጋጋሚ ቢጠቆምም አልፈለገም ወይም አልሆነለትም። ከዚህ አንፃር የኦነግን የመገንጠል አቋም ስንቃወም ለኦሮሞ ብሔር በኢትዮጵያዊነት ኩራቱና እምነቱ ለሰኮንድም ጥርጣሬ ሳይገባን መሆን ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ከማንም ባላነሰ የኦሮሞ ብሔር ሀገር ናት። ደምቶላታል። ቢበደልም ሀገሬ ብሎ ሞቶላታል። ይህን መስዋዕትነቱን መና ማስቀረትና ሚናውንና ታሪካዊ ቦታውን መሰረዝ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቱ ለመብቱ መታገል ነው ያለበት። የኦሮሞ ብሔር እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው። ድርጅቶቹ ነን የሚሉት ሊከተሉትና ድፍረቱ ሊኖራቸው ይገባል።

የሀገራችንን አንድነት ከሚፈታተኑት ኃይሎች አንዱ ሻቢያ ነው። የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የሕዝቧን አንድነት በተመለከተ ወያኔና ሻቢያ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽ ብቻ ሳይሆኑ ሁለቱም በመጀመሪያው ገጽታ ላይ ናቸው። እኚህ ሁለት ከፋፋዮች አምባገነን ባህሪያቸው ቢያባላቸውም በጥፋት ጎዳና ላይ እጅ ለእጅ መሆናቸው ጥርጣሬ ሊገባን አይገባም። ከጅምሩ ወያኔን ቀፍቅፎ የመገንጠል ሴራውን ስኬታማ ያደረገው ሻቢያ ዛሬ ደግሞ ኦነግንና ኦብነግን እጉያው አቅፎ ኢትዮጵያን በየአቅጣጫው ሊበታትናት ሥራዬ ብሎ ሲፈጋ የአንድነት ኃይሎች አንድነታችንን አጠንክረን ለመቋቋም ከመዘጋጀት ይልቅ እኛም ስንደረብላቸው

እጅጉን ያሳዝናል። ሻቢያን ተገን በማድረግ የምናገኘው ድል ቢኖር ዳግም የኢትዮጵያ አንድነትና ብሔራዊ ጥቅም ላይ ያነጣተረ ነው። ሻቢያ ጉያ እስከገባን ድረስ ሊያስቀምጣቸው የሚፈልጋቸውን ቅድም ሁኔታዎች መቀበልን ግድ ይላል። ስለ አሰብ ጉዳይ እንዳናነሳ እንታዘዛለን። ከኢትዮጵያ መገንጠል ግባቸው ከሆኑ ጋር እንድንተባበር እንጠየቃለን። የዚህና የሌሎች ቅድመ ሁኔታ ውጤት ነው አንዳንድ ድርጅቶችን የአነግ ጠበቃ ያደረገው። በሻቢያ በኩል የሚደረግ ድጋፍ አዋጪነት የለውም፡ ከታሪክ እንማር ቢባሉ አልሰማ ያሉት አንዳንድ ድርጅቶች ዛሬ የአንድነት ኃይሉን ወደ ጎን እየገፉ፡ በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ከሚዘምቱት ጋር እጅና ጓንት ሊሆኑ ሲነሱ ዛሬ ስለ ሀገር ያልተጮኸ መቼ ሊጮህ!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ የሚፈልገው መሠረታዊ ለውጥ ነው። መሠረታዊ ለውጥ ማለት በአፈና፡ በብዝበዛና በዘረኝነት ላይ የተመሰረተው አገዛዝ ወድሞ በቦታው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚወክል፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም የሚያስጠብቅ፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ዘዴ የተመረጠና በሕዝቡ ቁጥጥር ሥር የሆነ መንግሥት፡ የአስተዳደር፡ የፍርድና የሕግ አውጭነት ስልጣን ሲይዝ ነው።

ለውጥ ማለት የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ከመሠረቱ ሲነቀል ነው። ለውጥ ማለት የኢትዮጵያ መንግስት የባዕዳን ጥቅም ጠባቂና ጥገኛ መሆኑ ቀርቶ የብሔራዊ፡ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ዕቅድ ሁሉ በሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም መሠረት ሲታቀድና ሥራ ላይ ሲውል ነው። ለውጥ ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙት ብሔር/ብሔረሰቦች መካከል በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት የሚገነባበት ሕጋዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ባህላዊ መሠረት ሲጣል ነው። ለውጥ ማለት ባጭሩ በዘር፡ በሃይማኖት፡ በክልል፡ በብሔር/ብሔረሰብ ሲከፋፈል የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘረኞችን፡ አምባገነኖችን አገዛዝ ከመሠረቱ ገልብጦ የመንግሥት ሥልጣን በቁጥጥሩ ሥር አድርጎ፡ የዝርፊያን ልጓም በጥሶ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት መንገድ ሲከፍት ነው።

ሕዝብ የማይካፈልበት ለውጥ መሠረታዊ ለውጥ አይደለም። ገዥን መለዋወጥ እንጂ። የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን የሚሻውና የሚፈልገው አንዱን ወያኔ በሌላው መቀየር አይደለም። የሚፈልገው የማንም ተገዥ የማይሆንበትን፡ በማንም የማይረገጥበትን፡ አስተዳዳሪዎቹን በዴሞክራሲያዊ መንገድ እሱው እራሱ የሚመርጥበትና የሚቆጣጠርበት ሥርዓት ነው። ይህ ዓይነት ለውጥ የሚገኘው ደግሞ በትግል ነው። በአቋራጭ የሀገርን ጥቅምና እልውና ከሚፈታተኑ ጋር በመሞዳሞድና በመገለባበጥ አይሳካም። አይሰምርምም።

ትግል በቅድሚያ የሚታገሉትን ማወቅ ይጠይቃል። የሀገርና የሕዝብ ጠላት ማነው? የሚለውን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ወያኔና ሻቢያ ለጥያቄ የሚቀርቡ፡ በሀገር ጥቅምና በሕዝብ አንድነት ላይ የመጡ የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው። ከዚህ ተያይዞ በኢትዮጵያ አንድነት የማያምኑ፡ ከኢትዮጵያ መገንጠልን የሚያራምዱ፡ ጥያቄአቸውን በኢትዮጵያ አንድነት ሥር ሊያስተናግዱ ድፍረቱ የጎደላቸው የአንድነት ጠላቶች መሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል። ከነኚህ አንድም ሦስትም ከሆኑ የሀገር ጠላቶች ጋር ተገን ሆኖ የሚመጣ ለውጥ

*ለዳግም ጥፋት ሀገርና ሕዝብን ያዘጋጃል፤ የራስን እንጂ በምንም መልኩ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም አያስጠብቅም። የሕዝቡንም ጥያቄ አይመልስም።*

*በኢትዮጵያ መሠረታዊ ለውጥ ቢደረግ ከወያኔ አገዛዝ ጋር ያለአግባብ የሀገርን አንጡራ ሀብት የዘረፉና የደለቡ ሊያባንናቸው ይችላል። ሕዝብን ያለአግባብ አፈናቅለው መሬቱንና ቤቱን የዘረፉና፡ በልጆቹ ዕንባ ቱጃር የሆኑ ሕገ ወጥነታቸው እንቅልፍ ይነሳቸዋል። ለመብቱና ለነፃነቱ የጮኸውን ሕዝብና ልጆቹን ለስደት፡ ለእስር ከመዳረግ አልፈው ሕይወት የቀጠፉ፡ ስልጣናቸውን ተመክተው ነውና ሕዝቡም ሆነ የሕዝብ ወገን ለስልጣን ከሚበቃ በስሙ እየነገዱና እያስነገዱ፡ በለውጥ ስም ሌላ ተረኛ እያመጡ የሕዝብን መከራና ስቃይ ሊያራዝሙ ወደኋላ የማይሉ ናቸውና ይህን ሁሉ ጠመዝማዛ ጎዳና ለማለፍ ፍልሚያ ወሳኝ ነው። የለውጥ እንቅፋቶች በመሠረቱ ከአገዛዙ ባሻገር የአገዛዙ አስተሳሰብ ባሪያ በመሆን፡ የነሱን ተንኮልና አስተሳሰብ የሚያሰራጩ አንዳንድ አድርባይ ምሁራንንም ያጠቃልላል።*

*መሠረታዊ ለውጥ ለማካሄድ፡ ለውጡ ለምን እንደተፈለገ፡ ወይንም መለወጥ ያለባቸው ዋና ዋና ነገሮች የትኞቹ እንደሆኑ በትክክል ማወቅ ያስፈልጋል። ይህ አንዳንድ ግለሰቦችን በማስወገድ መሠረታዊ ለውጥ ተደረገ ብሎ ከማመን ያድናል። የኢኮኖሚ፡ የፖለቲካ መሰረቱን ሳይነኩ፡ ሞራላዊ ተሐድሶ እናካሂዳለን ከማለት ያድናል። ሕዝቡን ለትግል፡ ለአመጻ ያነሳሱት፡ ያስገደዱት፡ ምክንያቶች ሳይፈቱ ሕዝቡ አሜን ብሎ ያቅፈናል ወደሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ከመድረስ ያድናል። መሠረታዊ ለውጥ ለማድረግ የሀገራችንና የሕዝባችንን ዋና ዋና ችግሮች፡ ወቅታዊ የዓለም ሁኔታ ለይቶ ከማወቅ ሌላ፡ እነዚህ ችግሮች እንዴትና በማን ሊወገዱ እንደሚችሉ አተኩሮ ማስተዋልና ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።*

*መሠረታዊ ለውጥ በኢትዮጵያ ሕዝብና በዘረኛው ወያኔና አጃቢዎቹ መካከል የሚካሄደው የትግል ፍሬ ነው።*

*የኢትዮጵያ አንድነት ለዘላለም ይኑር!*

**ቸር ይግጠመን**

**አሉላ** (alulla2@yahoo.com)